ALL AMAHARA PEOLE'S RELIEF & DEVELOPMENT ASSOC
P.O.BOX 50127
Washington, DC 20001-0127
Tel- (202) 236-9436 Fax (301) 593-2787
Email - AAPRDA@Yahoo.com

# ውሸት ሲደጋገም እውነት ይይመስላል

ይህ አባባል ለወያኔዎችና ለሌሎች ፀረ-አማራ ብሔረሰቦች አልሰራላቸውም። ወያኔ በረሀ በነበረበት ጊዜ አማራውን የማስጠላት ዘመቻ የያዘው በይፋ ሳይሆን በካድሬዎቹና በደጋፊዎቹ መካከል ብቻ ነበር። እንዲህ እንደዛሬ ቢሆን ኖሮ የወሎን፣ የጎንደርን፣ የጎጃምንና የሰጎን ብትር አልፎ የምኒሊክን ቤተ መንግስት ለመያዝ ቀርቶ በህልሙም አያስበውም ነበር።

የወያኔ መንግስት ጭካኔ ዘረፋና ዘረኝነት ያንገሸገሸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዴሞክራሲ ምርጫ ራቁቱን ሲያስቀረው ለዚህ ምክንያት ያደረገው አማራው ስልጣኔን ሊጥልብኝ ነው በማለት በየቀበሌውና በየሴሚናሩ ላይ የየዕለት መፈክሩ ከማድረጉም በላይ ለሌሎች መንግስታትም ይህንኑ የውሸት ቀጠፋውን ቀጥሎበታል። በወያኔዎች አነጋገር የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በአማራነት ተፈርጇል ማለት ነው።

ቀደም ሲል ወያኔ ሕዝብን በማታለል ስልጣኑን በእጁ ካስገባ በኋላ አገር መገንጠልና ክፍለ ሐገሮችን በመቆራረስ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአለም ተወዳዳሪ የለውም ቢባል ከሀቅ የራቀ አይደለም። ለምሳሌ ለትግራይ ሕዝብ ከአጎራባቾቹ ከጎንደርና ከወሎ ክፍለ ሐገሮች መሬት በመቁረስ ሰጥቷል። ታዲያ የትግራይ ሕዝብ ዘለቄታ ሰላም አንዲያጣ ያደርገዋል እንጂ አይጠቅመውም። በሌላ በኩል ወያኔ ኤርትራ እንድትገነጠል የመጀመሪያው አላማው ስለነበር ግንጠላውን በተባበሩት መንግስታት አስፀደቀ።

ከጥቂት አመታት በኋላ ግን ያልነበረ የወሰን ጭቅጭቅ በማስነሳት አያሌ የኢትዮጵያ ወጣቶች ፈንጂ እያስረገጠ እንዲቃጠሉ አድርጓል። በዚህ አድራጎቱ የትግራይን ሕዝብ ጎረቤት አልባ አድርጎታል ማለት ይቻላል።

ከላይ በርዕሱ እንደገለጥነው የፀረ አማራ ቅስቀሳቸው በተቃራኒው የአማራውን በሳል አስተሳሰቡን፣ አገር ወዳድነቱን፣ ለዳር ድንበራችን ዘብ የቆመ መሆኑን ሀገሪቱ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር በባዕዳን እጅ እንዳትወድቅ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በግንባር ቀደምትነት በአዝማችነትና በዘማችነት የታወቀ ሕዝብ መሆኑን አንፀባረቀለት። የአሁኑ ትውልድም የወያኔን መንግስት የንብረት ዘረፋና የሽብር አስተዳደር በማየቱ የቀድሞይቱን ኢትዮጵያን በመዘከርና ወደፊት እንዴት መገንባት አለባት በማለት እያሰበ በመሆኑ ግንቦት ሰባት 1997 የወሰደው እርምጃ ማንም ሊያንቀሳቅሰው የማይችል መሠረት ነው።

በ1966 የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ምሁሩ፤ የተማረው፤ ሠራተኛው፤ ገበሬው፤ ነጋዴው፤ ወታደሩ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግስት የጣለው ፍትህ ዴሞክራሲና እኩልነት በሚል ነበር ከዳር እስከ ዳር የተነሳው። ይሁንና በጮሌ የበታች መኮንኖች የአንድነትና የዴሞክራሲ፤ የእኩልነት መሳሪያ የሆነው የሕዝብ ስልጣን ተነጠቀ። በጣም የሚገርመው በወቅቱ በአውሮፓና በሌሎች አገሮች ኢትዮጵያ የሚወዷትም የሚጠሏትም ወጣት ምሁራን ተሰባስበው ደርግን የተሳሳተ አቅጣጫ በማስያዝ በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች የሚገኙትን አማሮችና ሌሎችን ሕዝቦች ትጥቅ አስፈትተው ነበር። የጥላቻ መርዛቸውን በሰፊው ረጩት። ሳይውል ሳያድር የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈለገውንና የተመኘውን አላማ ሳይሆን ያገኘው ያላሰበውንና ያልጠበቀውን የተወሳሰበ ችግር አጋጠመው።

በጠቅላላ በአገሪቱ ውስጥ በዘር ሳይሆን በፖለቲካ ቡድን ልዩነት በሁሉም በኩል ምትክ ሊገኝላቸው የማይችሉ በሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ምሑራን እርስ በርሳቸው ተላለቁ። የሀገሪቱ ዳር ድንበር ተደፈረ፤ ገንጣይና አስገንጣዮችም አላማችን እውን የሚሆነው አሁን ነው በማለት የምሥራቁ ዳር ድንበር እንዲደፈር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርገው ነበር። ይህ የክህደት አድራጎታቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሲዘከር ይኖራል። ደርግም በርካታ ሚሊሺያ በማሰልጠን የተከበረውን ወሰን አስከበረ። ከዚያም ከገንጣዮችና አስገንጣዮች ጋር ሲፋለም ከመቆየቱ በስተቀር የኢትዮጵያ ሕዝብን ፍላጎት ለማሟላት አቅምና ብቃት ሳያገኝ ስልጣኑን ለገንጣዮችና አስገንጣዮች አሳልፎ ሰጠ። በዚያን ዘመን ወያኔ ስልጣን የተረከበው በባዕድ አገር አደራዳሪዎቹ ባዕዳን ነበሩ። የሥልጣኑ ተረካቢዎች ወያኔ ብቻ ሳይሆን ብዙ ሕዝብ እወክላለሁ የሚለው የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) እና ሌሎችም ነበሩ። ታዲያ ገንጣይና አስገንጣዮች በተስማሙበት ሰፊ ስልጣን የነበረውን ኦነግን በምን ዘዴ ከመንግስታዊ መዋቅር አስወጡት? ይህን ኦነግ የሚመልሰው ጥያቄ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብን እንወክላለን ብለው ዕድለ ትብብር ለጀመሩት ግን አቅጣጫቸውን እንዲመረምሩ አበክረን እናሳስባለን። ሻቢያ ለኢትዮጵያ ጥሩ ነገር ያስባል ብሎ መገመት ትልቅ ስህተት ወይም ፍፁም የዋህነት ነው። ከእባብ ዕንቁላል እርግብ እንደማይፈለፈል ከሻቢያ ለኢትዮጵያ ጥሩ ነገር አይታሰብም። ምናልባት ከሙቶ አመት የቤት ሥራ መካከል አስቸጋሪውና መርዛሙ ይህ ይሆን?

ትብብሩን እኛ ኢትዮጵያውያኖች እንደ ወያኔ በደፈናው አንጠላውም። እውነት አንዲት ኢትዮጵያ ለሕዝቦች እኩልነት፤ ፍትህ ነፃነትና ብልፅግና ከሆነ አላማውን ተግባራዊ ለማድረግ ምድራዊ ኃይል አያግደንም።

በዚህ አዲሱ "ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ" ተብሎ ለተሰየመው ድርጅት የፖለቲካ ራዕይ ወይም አላማ መሠረት የመላው አማራ ሕዝብ መረዳጃና የልማት ማሕበር ትብብሩ ወክለናቸዋል የሚሉትን ሕዝብ አላማና ፍላጎት የማይወክልና ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ የሆነ የፖለቲካ ግብ ያለው መሆኑን ተገንዝበናል።

ከትብብሩ የፖለቲካ ራዕይ ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ለምሳሌ የትብብሩ መጠቀሚያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው ብለዋል። የትብብሩ መስራች አባል የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወክየዋለሁ የሚለውን የኢትዮጵያ ኦሮሞ ሕዝብን ሳያማክር የኦሮሞን ቋንቋ ፊደል አፍሪካዊ ከዚያም ኢትዮጵያዊ ከሆነው የግዕዝ ፊደል ወደ ቅኝ ገዥዎች ፊደል

ወደእንግሊዝኛ መቀየራቸው ይታወሳል። አሁን ደግሞ በዚህ ትብብር ሰነድ መሠረት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቋንቋ ያለ ኢትዮጵያውያኖች ፍቃድ ከአማርኛ ወደእንግሊዝኛ ቀይረውታል። ይህ የሚያሳየው የአዲሱ የትብብር ፖለቲከኞች አምባገነንነትና ፀረ ዴሞክራሲያዊነት ነው።

በዚህ ትብብር ዓለማ ሰነድ መሠረት "ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ አባል የሆኑ ድርጅቶች ድርጅታዊ አላማቸውን ይዘው መንቀሳቀስ ይችላሉ" ይላል። እንደሚታወቀው ሁሉ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር፣ የኦጋዴን ነፃ አውጪ ድርጅትና የሲዳማ ነፃ አውጪ ድርጅት በቋንቋና በዘር ኢትዮጵያን ከፋፍለው በየፊናቸው ስልጣን ይዘው ወክለነዋል ከሚሉት ሕዝብ ፍላጎት ውጭ ለመግዛት ነው። ይህ ከሆነ መላ ኢትዮጵያን ወክያለሁ የሚለው ቅንጅት ለነዚህ ሦስት ዘረኛና ተገንጣይ ፖለቲከኞች መጠቀሚያ ሊሆን ነውን?

በዚሁ የትብብር አላማና መተዳደሪያ ደንባቸው ሰነድ "ኢትዮጵያና አካባቢዋ" እያሉ በየምዕራፉ ጠቅሰዋል። በOLF፣ ONLF፣ SLF የትግል አላማ መሠረት ኢትዮጵያና አካባቢዋ ሲሉ የነሱ ዘር ክልል አንድ አገር፣ የሌላው የዘር ክልል ሌላ አገር በዘር መደራጀት የማያምኑት ኢትዮጵያ ማለታቸው ይሆን? ኢትዮጵያና አካባቢ ከማለት ይልቅ ሁሉም ኢትዮጵያውያኖች ማለት አይቀልምን? ነው ወይንስ እነዚህ የዘር ፖለቲከኞች እንደልማዳቸው ፍትህ ዴሞክራሲና አንድነት የሚወደውን ሕዝብ ትግልና መስዋዕትነት ተጠቅመው የአንድ አገርን ሕዝብ በዘር በታትነው በሕዝብ ትከሻ ላይ ስልጣን ለመያዝ ያላቸውን ዕቅድ ከአሁኑ እየታያቸው ነው።

በትብብሩ ሰነድ መሠረት ትብብሩ የወያኔን ሕገ መንግስት እንቀበላለን ብለዋል። ኢትዮጵያ በዘርና ሃይማኖት ከፋፍሎ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር የሚያጋጨው በመሬት ይዞታ ላይ አምራቹን መሬት አልባ ያደረገውን በክልል ግዛት ምክንያት ገበሬውና ነጋዴው እንዲፈናቀልና እንዲዘረፍ ያደረገውን የወያኔ ሕገ መንግስት የሚቀበል ከሆነ ለምን ወያኔን ይቃወማሉ? ከወያኔ ጋር ያላቸው ችግር የሥልጣን ይዞታ ብቻ ነው ማለት ነው?

በጠቅላላው የመላው አማራ ሕዝብ ፀረ ወያኔ የሆነ የተቃዋሚዎች ትብብር ተፈጠረ የሚለውን ዜና ስንሰማ ደስ ብሎን ነበር። ነገር ግን የትብብሩን መተዳደሪያ ደንብና የአላማ ሰነድ ካነበብን በኋላ ትብብሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት የማያሟላ መሆኑን በተለያዩ መድረኮች ብንናገርም ሃሳባችንን በጽሑፍ ማስቀመጥ አስፈላጊ ስለሆነ በዚች አጭር ማስታወሻ ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

ታዲያ ታሪክ እራሷን ትደግማለች የሚለው አነጋገር እንደገና እንዳይደርስ መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ቅንጅት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ፍትህና እኩልነት የሚታገል ድርጅት ይመስለናል። ለዚህም ነው በግንቦቱ ምርጫ ዘመን ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ኢትዮጵያ የሕዝበ አመኔታ አግኝቶ ሊያሸንፍ የቻለው።

ይህን በብዙ ኢትዮጵያውያኖች ትግልና መስዋዕትነት የተገኘውን አመኔታ በዘረኞችና ተገንጠዮች የፖለቲካ ቡድኖች መጠቀሚያ እንዳይሆን የመላው አማራ ሕዝብ የርዳታና የልማት ማሕበር አስቀድሞ ያሳስባል።

የመላው አማራ ሕዝብ የዕርዳታና የልማት ማሕበር
ዋሽንግተን ዲ.ሲ.
July 14 2006